# እኔስ..... ተናገርኳት!

(አክሊሉ ሃይሉ)

ስምሽን አላስታውሰው፣ ደግሜ አልጥራበት፣
ስምሽ ነው ደመኛሽ፣ የእድሜ ልክሽ ጠላት።
ደምሽ ተንጠፍጥፎ፣ ይድረቅ ለወዲያኛው፣
እሱ ነው ስሪትሽ የዘርሽ መገኛው።
ማጠንሽም ይንጠፍ፣ ይምከን እንደ በቅሎ፣
እስከመቼ ድረስ፣ ስንቱን ጉድ አብቅሎ።

አንጀትሽ ተፈትቶ፣ ይበተን ከሜዳው፣
ከሆድሽ መሽጎ፣ ዘር እሚያጋምደው።
ልብሽን ሰንጥቀው፣ ይዩብሽ ጉድሽን፣
መውደድ ጥላቻሽን፣ ሐዘን ደስታሽን።
ያየር ከረጢትሽ፣ ትንፋስሽ ይቋረጥ፣
ነፍስ እያቋደሰ፣ ትውልዱን ከሚያስምጥ።

ክንድሽንም አጥፈው፣ ከደረት ይሰሩት፣
ሁሉን እያቀፈ፣.............
ስንቱን ከሚያዋትት፣ ስንቱን ከሚያሟግት።
እግርሽ ሽባ ይሁን፣.........
እርሻ አትሂጅበት ፣ ውሀም አትቅጅበት፣
ቃርሚያ እየሰበሰብሽ፣ ግርድ አታመርቺበት።

ስስት እማያውቀው፣ ይታሰር አንጀትሽ፣
ፈትፋችና አጉራሹ፣ ጣትሽ ነው ደመኛሽ።
የናትነት ጓዳሽ፣ ሴትነትሽ ይከዳሽ፣
ሴት በመሆንሽ ነው፣ የሚያንከራትትሽ።
ጆሮችሽ ይንተቡ፣ መስማት ያቅታቸው፣
ውርደትሽን መስማቱ፣ ላይን እንባ ቀለብ ነው።

አይንሽን ሾርበው፣ ይጋርዱት በሸማ፣
ምን ያደርግለታል፣ መብቱን ለተቀማ።
ማቀነትሽን ፈትተው፣ ያጥልቁልሽ ሱሪ፣
አሳብ ነው ልጅ መውለድ፣ አንች ድሃ! አዳሪ።
እኔም እናቴ አልበል፣ አንችም ልጄ አትበይኝ፣
ወፍዘራሽ ማንዘራሽ፣ የቲም ልጅ ከሆንኩኝ።

ቀብሬን ይማሱና፣ መርዶየን ይንገሩሽ፣
አንችም አታልቅሽ፣ እኔም ባይኔ አልይሽ።
የኔን ነገር ለሷ፣ ተዋት አትንገሯት፣
ወለደችኝ እንጅ፣ እኔ መች ወለድኳት።
የልቤ እንባ ፈሶ፣ አንጀቴን አራሰው፣
መውለድ ምን ያደርጋል፣ ልጅ እዬከዳው ሰው፣

መውለድ ክብር ሁኖ ፣ ወግ ማረግ ካልታዬ
በካር ምን መቅኖ አላት፣.........
ቤቷ ከደኸዬ፣ ሽሏ ከጎፈዬ፣ ክብሯ  ከጠኸዬ !!!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!

አመሰግናለሁ!